የሰበር መ.ቁ. 31640

የካቲት 11 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አመልካች፡- አቶ ገረመው ግዛው ከጠበቃ ተሾመ ደምሴ ጋር ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ፈቃዱ ያደቴ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው ተጠሪ በክስ የጠየቀውን ገንዘብ አመልካች የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት በበታች ፍ/ቤቶች በመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች ቅሬታ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ ተጠሪ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ ተከሣሽ የሠ.ቁ.1-07889 የሆነውን መኪና በነሐሴ 4 ቀን 1991 ዓ.ም በተፃፈ ውል በብር 34,000 (ሠላሣ አራት ሺህ) ሸጦልኝ መኪናውንም ያስረከበኝ ቢሆንም ስም ሣያዛውር በመቅረቱ ምክንያት ክስ አቅርቤበት በግንቦት 9 ቀን 1996 ዓ.ም ስም እንዲያዛውር ተወስኖበት ጉዳዩ በአፈፃፀም ላይ ይገኛል፡፡ የስም ዝውውሩን በተመለከተ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በይግባኝ ክርክር ላይ እያለን መኪናውን ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ትእዛዝ ከፍ/ቤቱ በመተላለፉ እስከ የካቲት 30 ቀን 1993 ዓ.ም መኪናውን ለማንቀሳቀስ ችዬ ነበር፡፡ ነገር ግን ከመጋቢት 1 ቀን 1993 ዓ.ም ይህ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ መኪናውን ማንቀሣቀስ ያልተቻለ ስለሆነና የመኪናውም የቀን ገቢ ብር 50 በ1710 ቀናት ሲባዛ በድምሩ ብር 85.500



(ሰማንያ አምስት ሺህ አምስት መቶ) ከወለድ ወጭና ኪሣራ ጋር ተከሳሽ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የከሣሽ ክስና ማስረጃም ለተከሣሽ ደርሶ በሰጠው መልስ በመካከላቸው የመኪና ሽያጭ ውል የተደረገ መሆኑን አምነው በፍ/ቤት ትእዛዝ እስከ የካቲት 30 ቀን 1993 ዓ.ም መኪናው ከተንቀሳቀሰ ከዚያ ወዲህም ቢሆንም ለፍ/ቤት አመልክቶ ማንቀሣቀስ እየቻለ በገዛ ፈቃዱ አቁሞት ከሆነ ተከሣሽ ኃላፊ ሊሆን አይችልም፡፡ እንደዚሁም ከሣሽ መኪናውን ከተረከበ 7 ዓመት ያለፈው ስለሆነ ውሉ ጉዳት አድርሷል በውሉ አፈፃፀም ጉዳት ደርሷል ሳይባል በውሉ መሠረት ስም እንዳዛውር በተወሰነው መሠረት ስም ከማዛወር በስተቀር ሌላ ዕዳ ለመክፈል የገባሁት ግዴታ ስለሌለ ክሱ ከኪሣራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መዝገቡን መርምሮ ለክሱ ምክንያት የሆነው (ታክሲ) መኪና ባለቤትነቱን ተከሣሽ በሕግ ተገደው በከሣሽ ስም እንዲያዛውሩ እስከተደረገበት ግንቦት 9 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ የመኪናው ባለቤትነት በተከሣሽ ስም ተመዝግቦ እንደነበር የሚታመን ሲሆን በመኪናው ላይ ቦሎ ለማስለጠፍ ደግሞ የመኪናው ባለንብረት መቅረብ እንዳለባቸውና ተሽከርካሪውን ለምርመራ ክፍሉ በማሣየት ማስመርመር እንደሚገባቸው የተረጋገጠ ሲሆን ተከሣሽ ግን ይህን ባለማድረጋቸው ተሽከርካሪው ሊንቀሣቀስ ያልቻለ በመሆኑ በከሣሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ ናቸው ካለ በኂላ መኪናው ያለ ሥራ የቆመበትን የ3 ዓመት ከ2 ወር ከ9 ቀን በድምሩ ብር 57.450 (አምሣሰባት ሺህ አራት መቶ ሃምሣ) ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተውም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

ይህ ሰበር ሰሚ ችሎትም የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ካሣራ ሊከፍል ይገባል በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባው መሆኑን በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ኪሣራ ሊከፍል ይገባልን? የሚለው በመሆኑ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የጉዳት ኪሣራ ጥያቄ ከውልም ሆነ ከውል ውጭ ባለ ግንኙነት ላይ ተመሥርቶ ሊቀርብ የሚችል ሲሆን ከውል ጋር በተያያዘ የሚቀርብ የጉዳት ኪሣራ ጥያቄ የሚመዘነው ውሉ በአግባቡ ተፈጽሞ ቢሆን ኖሮ ጥያቄ አቅራቢው ሊኖረው ከሚችለው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ጋር ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል በመኪና ሽያጭ ውል ላይ ተመሥርቶ የነበረ ግንኙነት ተቋቁሞ እንደነበር የተረጋገጠ ሲሆን በዚሁ ውል መሠረትም የመኪናው ገዢ የሆኑት የአሁን ተጠሪ ሻጩ (አመልካች) ባለቤትነቱን በስሜ ያላዛወረ ስለሆነ እንዲያዛውር ይወሰንልኝ የሚል አቤቱታ ለፍ/ቤት አቅርበው ይሄው አቤቱታም በፍ/ቤት ተቀባይነት አግኝቶ ሻጭ የመኪናውን ባለሀብትነት በገዢው ስም ሊያዛውሩ ይገባል በማለት ፍ/ቤቱ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩልም አመልካች ስም ማዛወር እንደሚገባቸው በፍርድ የተወሰነ ቢሆንም በውል ግዴታ ውስጥ ባለዕዳ የሆነው ወገን የጉዳት ኪሣራ ከፋይ የሚሆነው ውሉን አሟልቶ ሣይፈጽም ሲቀር ወይም ውሉን ከስምምነቱ ውጭ አዘግይቶ በመፈፀሙ የተነሣ በሌላው ተዋዋይ ወገን ላይ በገንዘብ የሚተመን ኪሣራ የደረሰ መሆኑ ሲረጋገጥ እንደመሆኑ መጠን አመልካች ስም የማዛወር ኃላፊነት አለበት ተብሎ ውሣኔ የተሰጠ ቢሆንም የሽያጭ ውሉ በተደረገ ጊዜ የመኪናው ባለቤትነት የተመዘገበው በሻጭ በአሁን አመልካች ስም ሣይሆን በሌላ ግለሰብ ስም መመዝገቡን ተጠሪ ያውቅ



እንደነበር ሻጭም መኪናውን ለመሸጥ የሚያስችል የውክልና ሥልጣን የነበረው ስለመሆኑ ገዢው (ተጠሪ) አረጋግጦ ግዢውን እንዳልፈፀመ መገንዘብ የተቻለ ከመሆኑም በላይ አመልካች የመኪናውን ባለሀብትነት በተጠሪ ስም ለማዛወር የበኩሉን ጥረት አድርጎ ነገር ግን በተጠሪ አለመቅረብና አለመከታተል ምክንያት የስም ዝውውሩ ተግባራዊ ሊሆን እንዳልቻለም ተረጋግጧል፡፡

የስም ዝውውሩ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው በሻጩ ቀጥተኛ የውል ፈፃሚነት (specific performance) ብቻ የሚከናወን ሣይሆን የገዥውም ድጋፍ ታክሎበት ለውጤት የሚበቃ በመሆኑ በዚሁ መሠረት የበኩሉን አስፈላጊ ድጋፍ ተጠሪ ለአመልካች በመስጠት ስም እንዲዛወር ማድረግ ሲገባው ይህንን ባልፈፀመበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ኪሣራ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ በፍ/ብሔር ሕጉ ውልን አለመፈፀምንና የጉዳት ኪሣራ አከፋፈልን አስመልክቶ በቁጥር 1771 እና ተከታዮቹ ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ጋር የተገናዘበ ባለመሆኑ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 11081 በጥቅምት 2 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 50188 በሰኔ 13 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበባቸው ስለሆነ በፍ.ብ.ሕ.ሥ.ሥ.ቁ. 348(1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ኪሣራ ሊከፍል አይገባም በማለት ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ነ/ዓ